# ሒሳብ

## የ መምህር መምርያ መጽሐፍ

## 4ኛ ክፍል

አዘጋጆች፡-

ውብቱ ጫኔ (M.Sc.)
ፀጋዬ ሀይሉ (M.Sc.)
በለጠ ሁሉምታዬ (B.Sc.)

ገምጋሚዎች
ሙስጠፋ ከድር
ሮዳስ ድሪባ
ገስጥ አሰፋ

ሌይ አውት እና ኢሉስተሬሽን ዲዛይን፡-
ግርማ ዳርጌ
ኃይለጊዮርጊስ ተመስገን

አስተባባሪ
ጌታቸው ታለማ አጥናፉ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

© 2015 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ጥቅሶችና ሥዕሎች በምንጭነት
የተጠቀመባቸውን ሁሉ እናመሰግናለን፡፡

## ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣ በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለስራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን ፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## ሙሉ ቁጥሮች

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ 20

## መግቢያ

ተማሪዎች በሶስተኛ ክፍል እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብ፣ ማወዳደር፣ በቅደም ተከተል ማስቀመጥን እንዲያስታውሱ የተለያዩ ጥያቄዎች በቡድን እና በግል በመስጠት ለተማሪዎቹ ይከልሱላቸው። በአራተኛ ክፍል ደግሞ እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብ፣ መፃፍ፣ ማወዳደር፣ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣ የ1,000፣ 10,000 እና 100,000 ብዜቶች፣ ቁጥሮችን በቤት ዋጋቸው ማጠጋጋት፣ የኢትዮጵያ (የግዕዝ) ቁጥሮችን እንደሚማሩ ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል።

### የመማር ውጤቶች፣ ከዚህ ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች፡-

- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ይረዳሉ።
- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደርና በቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ።
- ሙሉ ቁጥሮችን መሰረት ያደረገ የዕለት ተዕለት ተግባራዊ መልመጃዎችን ይፈታሉ

## ትምህርቱን ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሳርያዎች

ይህንን ምዕራፍ ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሳሪያዎች የቁጥር ቤት ሰንጠረዥ፣ እርሳስ፣ ጠመኔ፣ የስዕል ወረቀት፣ ክላሰር፣ ማርከር፣ የቁጥሮች አቅራብ ዋጋዎችን አፈላለግ የሚያሳይ በትልቅ ወረቀት ላይ የተፃፈ፣ የኢትገዮጵያ ቁጥር የያዘ በትልቅ ወረቀት የተሰራ ዋና ዋናዎቹ በዚህ ምዕራፍ የምንጠቀማቸው መርጃ መሳሪያዎች ናቸው።

## 1.1 ሙሉ ቁጥሮችን በ1,000፣ 10,000 እና 100,000 መቁጠር

ክፍለ ጊዜ 4

### 1.1.1 የንዑስ ምዕራፍ የመማርያ ብቃቶች

- ሙሉ ቁጥሮችን በ1,000፣ 10,000 እና በ100,000 መቁጠር።

### 1.1.2 ንዕስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴዎችና ተግባራት

በመጀመሪያ በተግባር 1 ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጉ:: ጥያቄዎቹን ተወያይተው ሲጨርሱ ለተወሰኑ ቡድኖች መስጠት እና ከየቡድኑ አንድ አንድ ተማሪ ወጥተው እንድያስረዱ ያድርጓቸው:: በመጨረሻ እስከ 10,000 ያሉ መሉ ቁጥሮችን እንዴት እንደሚያነቡ፣ እንዴት እንደሚፅፍ፣ እንዴት እንደሚያወዳድሩ የቁጥር ቤት በመጠቀም ምሳሌዎችን ማስረዳት:: በተጨማሪ ከመልመጃ 1 ውስጥ የተወሰኑ ጥያቄዎች የክፍል ስራ በመስጠት ያርሙላቸው::

### 1.1.3 የምዘና ስልቶች

- ❖ ተማሪዎች ጥቁር ሰሌዳ ላይ ወጥተዉ እንዲሰሩ ማድረግ::
- ❖ የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ መስጠት እና የተግባር ስራ መስጠት
- ❖ የቃል ወይም የወረቀት ጥያቄዎችን ሙከራ መስጠት::
- ❖ የተማሪዎች የመማር ዉጤት እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት::

### 1.1.4 የተግባርና የመልመጃ መልሶች ከነማብራሪያቸው

#### የተግባር 1 መልሶች

1. የመጀመሪያው 10,000 ነው::
2. 10,000፣ 20,000፣ 30,000፣40,000፣ 50,000፣ 60,000፣ 70,000
3. 110,000: አንድ መቶ አስር ሺ: 100,000+10,000: 1 አስር ሺ እና 0 አንድ ሺ

#### የመልመጃ 1 መልሶች

1\.

← | 10,000 | 20,000 | 30,000 | 40,000 | 50,000 | 60,000 | 70,000 | →

ሀ 50,000፣ 60,000፣ 70,000፣ 80,000፣ 90,000

ለ 80 ሺ፣ 81 ሺ፣ 82 ሺ፣ 83 ሺ፣ 84 ሺ

3. 120,000፣ 20,000፣ 25,000፣
4. 55,000፣ 56,000፣ 57,000፣ 58,000፣ 59,000፣ 60,000፣ 61,000፣ 62,000፣ 63,000፣ 64,000፣ 65,000
5. 800,000
6. 

← | 50,000 | 60,000 | 70,000 | 80,000 | 90,000 | 100,000 | 110,000 | →

## የተግባር 2 መልሶች ፡-

1.

ሀ 155,762፡ አንድ መቶ አምሳ አምስት ሺ ሰባት መቶ ስልሳ ሁለት

ለ 348,139፡ ሶስት መቶ አርባ ስምንት ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ

ሐ 420,685፡ አራት መቶ ሀያ ሺ ስድስት መቶ ሰማንያ አምስት

መ 847,348፡ ስምንት መቶ አርባ ሰባት ሺ ሶስት መቶ አርባ ስምንት

2.

ሀ 828,719

ለ 563,438

## የመልመጃ 2 መልሶች

1. ሀ 843,976፡ ስምንት መቶ አርባ ሶስት ሺ ዘጠኝ መቶ ሰባ ስድስት

ለ 289,621፡ ሁሉት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ ስድስት መቶ ሀያ አንድ

ሐ 999,901፡ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ አንድ

2. በአሀዝ

ሀ 82,004፤ ለ 159,238፤ ሐ 400,010፤ መ 632,579

በሰንጠረዥ

| 100 ሺ | 10 ሺ | 1 ሺ | 100 | 10 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| | 8 | 2 | 0 | 0 | 4 |
| 1 | 5 | 9 | 2 | 3 | 8 |
| 4 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 |
| 6 | 3 | 2 | 5 | 7 | 9 |

3. ሀ $500{,}000 + 40{,}000 + 6{,}000 + 800 + 60 + 5$

ለ $300{,}000 + 60{,}000 + 8{,}000 + 500 + 0 + 9$

ሐ $900{,}000 + 00{,}000 + 9{,}000 + 200 + 30 + 7$

መ $200{,}000 + 10{,}000 + 8{,}000 + 100 + 30 + 2$

4. ሀ $900{,}000 + 80{,}000 + 5{,}000 + 400 + 70 + 5 = 985{,}475$

ለ $300{,}000 + 40{,}000 + 6{,}000 + 400 + 60 + 8 = 346{,}468$

5. 600,000፤ 700,000፤ 800,000፤ 900,000፤ 1,000,000

## በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች የተዘጋጁ መልመጃዎች

1. ቀጥሎ በአሀዝ የተፃፍትን ሙሉ ቁጥሮች በፊደል ፃፉ፡፡

   ሀ 586 ለ 4,935 ሐ 9,400 መ 8,397

2. ቀጥሎ በፊደል የተፃፉትን ሙሉ ቁጥሮች በአሀዝ ግለፁ፡፡

   ሀ. አንድ ሺ ሰባት መቶ አስራ ሁለት

   ለ. ስምንት ሺ ሰማንያ አራት

   ሐ. ዘጠኝ ሺ አራት መቶ ሰባ አምስት

   መ. ሶስት ሺ አራት መቶ ስልሳ ስምንት

## ፈጣን ለሆኑ ተማሪዎች የተዘጋጁ መልመጃዎች

1. ቀጥሎ በመተንተን ለቀረቡት ሙሉ ቁጥሮች የሚወክላቸውን ቁጥር በአሀዝ እና በፊደል ፃፉ፡፡

   ሀ. $1 \times 10{,}000 + 0 \times 1{,}000 + 0 \times 100 + 0 \times 10 + 0 \times 1$

   ለ. $2 \times 1{,}000 + 0 \times 100 + 4 \times 10 + 0 \times 1$

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዶ ቦታውን የሚወክሉ ሙሉ ቁጥሮችን ፃፉ

   ሀ $______ \times 1{,}000 + ______ \times 100 + _ \times 10 + ______ \times 1 = 9{,}002$

   ለ $3 \times ________ + ____ \times 100 + _ \times 10 + 3 \times __ = 3{,}643$

   ሐ $8 \times _______ + ____ \times 1 = 8{,}001$

   መ $_____ \times 1{,}000 + 3 \times _____ + ___ \times 10 + 5 \times _______ = 7{,}395$

## በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች የተዘጋጁ መልመጃዎች

1. በ10,000 እና በ16,000 መካከል የሚገኙ ሙሉ ቁጥሮችን በ1,000 ልዩነት በመዘርዝር ፃፉ

## ፈጣን ለሆኑ ተማሪዎች የተዘጋጁ መልመጃዎች

1. የሚከተለውን ሰንጠረዥ ሙሉ

| + | 1 | 30 | 70 | 100 | 2,400 | 96,000 | 100,000 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 10,000 | | | | | | | |

## በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች የተዘጋጁ መልመጃዎች

1. በ100,000 እና 600,000 መካከል የሚገኙ ሙሉ ቁጥሮችን በ100,000 ልዩነት በመዘርዝር ፃፉ፡፡

## ፈጣን ለሆኑ ተማሪዎች የተዘጋጁ መልመጃዎች

2. የሚከተለውን ሰንጠረዥ ሙሉ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| + | 8 | | 600 | | 10,000 | |
| 100,000 | | 100,025 | | 101,000 | | 1,000,000 |

## 1.2 የቁጥር ቤት ዋጋ በባላ 6 እና በላይ ሆሄ ሙለ ቁጥሮች

**የተግባርና የመልመጃ መልሶች**

**ክፍለ ጊዜ 4**

### 1.2.1 የንዑስ ርዕስ የመማር ብቃቶች፡-

- ባለ 6 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች የቤት ዋጋ ማንበብ ።
- ባለ 6 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች በመትንትን ማስቀመጥ።
- ባለ 6 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች የቤት ዋጋቸውን ማንበብና መፃፍ።

### 1.2.2 ንዕስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር

ተማሪዎች ምን ያህል እንደሚያስታውሱ ለመለየት በተግበር 4 ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቡድን ተወያይተው ሲጨርሱ ለተወሰኑ ቡድኖች እድል መስጠት እና ከቡድኖቹ አንድ አንድ ተማሪዎች ወጥተው እንዲያስረዱ ማድረግ እና ማበረታታት። ለተማሪዎች ግልፅ ያልሆኑላቸው ጥያቄዎች ካሉ ማብራሪያ መስጠት። ባለ 6 ሆሄ ሙሉ ቀጥሮችን እንዴት የቤት ዋጋ እንደሚለዩ የቁጥር ቤት ሰንጠረዥ በመጠቀም ምሣሌዎች ማሳየት ያስፈልጋል። በተጨማሪ ከመልመጃ 4 ውስጥ የተወሰኑ ጥያቄዎች በመምረጥ የቤት ስራ መስጠት እና ተማሪዎቹ የቤት ስራቸውን በትክክል መስራታቸዉን ማረጋገጥ።

### 1.2.3 የምዘና ስልት

- ባለ 6 ሆሄ ሙሉ ቁጥር በመስጠት የእያንዳንዱን ሆሄ የቤት ዋጋቸውን እንዲያስቀምጡ ጥያቄ መጠየቅ እና የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ፣ የቡድን ስራ ጥያቄዎችን መስጠት።
- ተማሪዎች ጥቁር ሰሌዳ ላይ ወጥተዉ እንዲሰሩ ማድረግ።
- የተግባር ስራ መስጠት።
- የቃል ወይም የወረቀት ጥያቄዎችን ሙከራ መስጠት።
- የተማሪዎች የመማር ዉጤት እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ-መልስ መስጠት።

## 1.2.3 የተግባርና የመልመጃ መልሶች ከነማብራሪያቸው

### የተግባር 3 መልሶች

1. ሀ እና መ ባለ ስድሰት ሆሄ ሲሆኑ  ነገር ግን ለ እና ሐ ባለ አምስት ሆሄ ነው

### መልመጃ 3 መልሶች

1. ሀ. 8 የመቶ ሺ ቤት ነው  ለ. 5 የአስር ሺ ቤት ነው ሐ. 4 የመቶ ቤት ነው
2. ሀ. 4 መቶ ሺዎች 6 አሰር ሺዎች 9 ሺዎች 4 መቶዎች 3 አስሮች 5 አንዶች

   ለ 3 አሰር ሺዎች፣ 2 መቶዎች፣ 8 አስሮች እና 9 አንዶች

   ሐ 3 አሰር ሺዎች፣ 7 ሺዎች፣ 6 መቶዎች፣ 4 አስሮች እና 5 አንዶች
3.

| ተ/ቁ | የመቶ ሺ ቤት | የአስር ሺ ቤት | የሺ ቤት | የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | 3 | 2 | 1 | 4 | 6 | 5 |
| ለ | 7 | 0 | 2 | 3 | 8 | 6 |
| ሐ | 2 | 4 | 8 | 6 | 4 | 7 |

### በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች የተዘጋጁ መልመጃዎች

1. ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ከጎን የተሰጡት ቁጥሮች የስንት ቤት ዋጋ እንደሚያመለክቱ ፃፉ፡፡

   ሀ. ከሙሉ ቁጥር 903,045 ውስጥ የ9 የቤት ዋጋ ስንት ነው?

   ለ. ከሙሉ ቁጥር 732,789 ውስጥ የ3 የቤት ዋጋ ስንት ነው?

### ፈጣን ለሆኑ ተማሪዎች የተዘጋጁ መልመጃዎች

1. በሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ ያሉትን መቶ ሺዎች፣ አስር ሺዎች፣ ሺዎች፣ መቶዎች፣ አስሮችና አንዶች ለይታችሁ ፃፉ

   ሀ. 87,139   ለ. 349,036

## 1.3 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

**የተመደበዉ ክ/ ጊዜ 4 ክፍለ ጊዜ**

### የንዑስ ርዕስ የመማር ብቃቶች:-

- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር።
- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ።

### ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴና ተግባራት

ተማሪዎች በተግበር 4 ላይ የሚገኙ ጥያቄዎችን በቡድን እንዲወያዩባቸው እና ጥያቄዎቹን ተወያይተው ሲጨርሱ ለተወሰኑ ቡድኖች እድል በመስጠት ከቡድኖቹ አንድ አንድ ተማሪዎች ወጥተው እንዲሰሩ ማድረግ ተገቢ ነዉ።

### የምዘና ስልት

- ተማሪዎች እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር እና በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ እና የቡድን ስራ መስጠት።
- ተማሪዎች ጥቁር ሰሌዳ ላይ ወጥተዉ እንዲሰሩ ማድረግ።
- የተግባር ስራ መስጠት።
- የቃል ወይም የወረቀት ጥያቄዎችን ሙከራ መስጠት።
- የተማሪዎች የመማር ዉጤት እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት።

### የተግባርና የመልመጃ መልሶች ከነማብራሪያቸው

#### ተግባር 4 መልሶች

1. ሀ. 834,028 > 823,879

   ለ. 734,028 < 734,079

#### የመልመጃ 4 መልሶች

1.

ሀ. 654,126___<___679,368

ለ. 900,008___>___900,004

ሐ. 69,682___<____694,657

መ. 328,414_>_____328,413

ሠ. 592,367__=_____592,367

2. ሀ ትልቁ 668,480

   ትንሹ 623,942

   ለ ትልቁ 946,948

   ትንሹ 946,250

3. ሀ ከትንሹ ወደ ትልቁ

   346,528፣ 442,251፣ 446,675፣ 523,947፣ 568,489

   ከትልቁ ወደ ትንሹ

   568,489፣ 523,947፣ 446,675፣ 442,251፣ 346,528

   ለ. ከትንሹ ወደ ትልቁ

   742,258፣ 768,480፣ 846,674፣ 923,842፣ 946,529

   ከትልቁ ወደ ትንሹ

   946,529፣ 923,842፣ 846,674፣ 768,480፣ 742,258

   ሐ. ከትንሹ ወደ ትልቁ

   546,247፣ 546,251፣ 546,482፣ 546,528፣ 546,875

   ከትልቁ ወደ ትንሹ

   546,875፣ 546,528፣ 546,482፣ 546,251፣ 546,247

### በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች የተዘጋጁ መልመጃዎች

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትንሹ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡

   ሀ 846,675፣ 846,489፣ 846,528

   ለ 568,675፣ 568,689፣ 568,690

### ፈጣን ለሆኑ ተማሪዎች የተዘጋጁ መልመጃዎች

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትንሹ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡

   ሀ 846,675፣ 846,489፣ 846,528፣ 846,947፣ 846,251፣ 823,947

   ለ 568,675፣ 568,689፣ 568,690፣ 568,677፣ 568,680፣ 546,529

## 1.4 ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸዉ ማጠጋጋት

### የተመደበዉ ክፍለ ጊዜ 3

### የንዑስ ርዕስ የመማር ብቃት፡-

➢ ሙሉ ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ማጠጋጋት፡፡

## ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴና ተግባራት

ተማሪዎች በተግበር 8 ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች በቡድን ማወያየት እና ጥያቄዎቹን ተወያይተው ሲጨርሱ አንድ አንድ ተማሪ ወጥቶ/ታ እንዲያስረዳ/ታስረዳ ያድርጉ። በተጨማሪ ከመልመጃ 8 ውስጥ የተወሰኑ ጥያቄዎች በመምረጥ የቤት ስራ፣ የክፍል ስራ መስጠት ተገቢ ነዉ።

### የምዘና ስልት

- ተማሪዎች ሙሉ ቁጥሮችን ወደ ተለያዩ የቤት ዋጋ እንዲያጠጋጉ የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ እና የቡድን ስራ መስጠት።
- ተማሪዎች ጥቁር ሰሌዳ ላይ ወጥተዉ እንዲሰሩ ማድረግ።
- የተግባር ስራ መስጠት።
- የቃል ወይም የወረቀት ጥያቄዎችን ሙከራ መስጠት።
- የተማሪዎች የመማር ዉጤት እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ-መልስ መስጠት።

### የተግባርና የመልመጃ መልሶች ከነማብራሪያቸው

#### የተግባር 5 መልሶች

1. ሀ. ወደ 10     ለ. ወደ 300     ሐ. ወደ 7,000
2. ወደ አስር ቤት ሲጠጋጋ፡ 149 ~ 150

   ወደ መቶ ቤት ሲጠጋጋ፡ 149 ~ 100

#### የመልመጃ 5 መልሶች

1. ሀ. ወደ አሰር ቤት ሲጠጋጋ፡ 6,839 ~ 6,840

   ወደ መቶ ቤት ሲጠጋጋ፡ 6,839 ~ 6,800

   ለ. ወደ አሰር ቤት ሲጠጋጋ፡ 955 ~960

   ወደ መቶ ቤት ሲጠጋጋ፡ 955 ~1,000

   ሐ ወደ አሰር ቤት ሲጠጋጋ፡ 8,462 ~8,460

   ወደ መቶ ቤት ሲጠጋጋ፡ 8,462 ~8,500

   መ ወደ አሰር ቤት ሲጠጋጋ፡ 18,132 ~18,130

   ወደ መቶ ቤት ሲጠጋጋ፡ 18,132 ~18,100
2. ሀ ወደ አንድ ሺ ቤት ሲጠጋጋ፡ 46,462 ~ 46,000

   ወደ አሰር ሺ ቤት ሲጠጋጋ፡ 46,462 ~50,000

ለ ወደ አንድ ሺ ቤት ሲጠጋጋ፡ 68,308 ~ 68,000

ወደ አሰር ሺ ቤት ሲጠጋጋ፡ 68,308 ~70,000

ሐ ወደ አንድ ሺ ቤት ሲጠጋጋ፡ 82,645 ~ 83,000

ወደ አሰር ሺ ቤት ሲጠጋጋ፡ 82,645 ~80,000

መ ወደ አንድ ሺ ቤት ሲጠጋጋ፡ 28,657 ~ 29,000

ወደ አሰር ሺ ቤት ሲጠጋጋ፡ 28,657 ~30,000

3. ሀ ወደ መቶ ሺ ቤት ሲጠጋጋ፡ 446,067 ~ 400,000

ለ ወደ መቶ ሺ ቤት ሲጠጋጋ፡ 634,365 ~ 600,000

ሐ ወደ መቶ ሺ ቤት ሲጠጋጋ፡ 978,564 ~ 1,000,000

መ ወደ መቶ ሺ ቤት ሲጠጋጋ፡ 258,798 ~ 300,000

4. ወደ አሰር ሺ ቤት ሲጠጋጋ፡ 153,602 ~ 150,000

ወደ መቶ ሺ ቤት ሲጠጋጋ፡ 153,602 ~ 200,000

**በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች የተዘጋጁ መልመጃዎች**

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ወደ 10,000፣ 1,000 እና 100 ቤት አጠጋጉ፡፡

ሀ 946,063 ለ 765,365

**ፈጣን ለሆኑ ተማሪዎች የተዘጋጁ መልመጃዎች**

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ወደ 100,000፣ 10,000 ፣1000 ፣ 100 እና10 ቤት አጠጋጉ፡፡

ሀ 946,063 ለ 765,365

## 1.5. ቁጥሮች

**የተመደበዉ ክ/ጊዜ፡- 5 ክፍለ ጊዜ**

**የንዑስ ርዕስ የመማር ብቃቶች፡-**

- የቁጥሮችን ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- የተለያዩ አገራት ቁጥሮችን ይለያሉ፣ ይፅፋሉ፡፡
- 1–100 ያሉ እና ከ 100 በላይ ያሉ የኢትዮጵያ ቁጥሮችን ያነባሉ፣ ይፅፋሉ፡፡

**ንዕስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴና ተግባራት**

በተግባር 6 ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቡድን እንዲ ወያዩባቸው በማድረግ ጥያቄዎቹን ተወያይተው ሲጨርሱ ለተወሰኑ ተማሪዎች እድል በመስጠት ወጥተው እንዲያስረዱ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎቹ ካስረዱ በኋላ ማበረታታት እና ለተማሪዎች ግልፅ ያልሆነላቸውን ጥያቄ ማብራሪያ ይስጡበት፡፡ በትልቅ ወረቀት ላይ የተፃፉ ከ1 – 100 እና ከ 100 በላይ ያሉ የኢትዮጵያ ቁጥሮችን በመጠቀም ምሳሌዎችን በመስጠት ማስረዳት፡፡ በተጨማሪ ከመልመጃ 9 ውስጥ የተወሰኑ ጥያቄዎች በመምረጥ የክፍል ስራ እና የቤት ስራ መስጠት ተገቢ ነዉ፡፡

## የምዘና ስልት

ተማሪዎች የኢትዮጵያ ቁጥሮችን እንዲያነቡና እንድፅፍ ምዘና መስጠት እና የተለያዩ የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ፣ የቡድን ስራ በማዘጋጀት መስጠት፡፡
ተማሪዎች ጥቁር ሰሌዳ ላይ ወጥተዉ እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ የተግባር ስራ መስጠት፡፡ የቃል ወይም የወረቀት ጥያቄዎችን ሙከራ መስጠት፡፡ የተማሪዎች የመማር ዉጤት እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

## የተግባርና የመልመጃ መልሶች ከነማብራሪያቸው

### የተግባር 6 መልሶች

1. **ቁጥር** ማለት ለመቁጠር ወይም ደግሞ ለመለካት የምንጠቀምበት የሂሳብ ቁስ ነው፡፡

### መልመጃ 6 መልሶች

1. የተለያዩ መልሶች ይጠበቃሉ፡፡ ለምሳሌ
   - የኢትዮጵያ ቁጥሮች:
     ፩፣ ፳፣ ፴፣ ፺፣ ፻
   - ሕንዳዊ-አረባዊ ቁጥሮች:
     500፣ 600፣ 700፣ 800፣ 900
   - የሮማውያን ቁጥሮች:
     V፣ X፣ L፣ C፣ D

2. ሀ MD = አንድ ሺ አምስት መቶ ለ CD =አራት መቶ ሐ MM = ሁለት ሺ
   መ ፸፯፻፬ = ሰባት ሺ ሰባት መቶ አራት
   ሠ ፵፬፻፵፬ = አራት ሺ አራት መቶ አርባ አራት
   ረ ፶፭፻ = አምስት ሺ አምት መቶ

### የተግባር 7 መልሶች

1. የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ፩፣ ፪፣ ፫፣ ፬፣ ፭
2. ሀ ፩- አንድ ለ ፭- አምስት ሐ ፱- ዘጠኝ
   መ ፲- አስር ሠ ፴- ሰላሳ ረ ፻- አንድ መቶ

## የመልመጃ 7 መልሶች

1. ሀ ፲፬-አስራ አራት ለ ፳፭-ሃያ አምስት ሐ ፴፮- ሰላሳ ስድስት መ ፵፬-አርባ አራት ሠ ፶፭-አምሳ አምስት ረ ፷፮-ስድሳ ስድስት ሰ ፸፯- ሰባ ሰባት ሸ ፹፰-ሰማንያ ስምንት ቀ ፺፱-ዘጠና ዘጠኝ
2. ሀ ዘጠና አንድ- ፺፩ ረ አርባ አምስት- ፵፭
   ለ ሰማንያ ሁለት- ፹፪ ሰ ሰላሳ አንድ- ፴፩
   ሐ ሰባ ሶስት- ፸፫ ሸ ሃያ ሶስት- ፳፫
   መ ስድሳ አራት- ፷፬ ቀ አስራ ሁለት- ፲፪
   ሠ አምሳ ስድስት -፶፮ በ አንድ መቶ- ፻
3. ፺፷

### በዝግታ ለሚረዱ ተማሪዎች የተዘጋጁ መልመጃዎች

ሀ. ፳ ለ. ፷ ሐ. ፺

### ፈጣን ለሆኑ ተማሪዎች የተዘጋጁ መልመጃዎች

የሚከተሉትን የኢትዮጵያ ቁጥሮች በፊደል ፃፉ ::

ሀ ፳፬ ለ ፶፫ ሐ ፸፮ መ ፺፬ ሠ ፷፫

## የተግባር 8 መልሶች

1. ፬፻፣ ፺፻፣ ፮፻፣ ፪፻
2. ሀ ፱፻: ዘጠኝ መቶ ሐ ፲፻: አንድ ሺ
   ለ ፭፻: አምስት መቶ መ ፼: አስር ሺ ሠ ፰፻: ስምንት መቶ

## መልመጃ 8

1. ሀ ፲፻: አንድ ሺ ሐ ፴፻: ሶስት ሺ
   ለ ፳፻: ሁለት ሺ መ ፬፻: አራት መቶ ረ ፷፻: ስድስት ሺ
2. ሀ አስር ሺ ፡ ፼ መ. አራት ሺ አንድ መቶ ሰባ ፡ ፵፩፻፸
   ለ ሰባ ሺ ፡ ፸፻ ሠ. ስምንት ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ: ፹፪፻፴
   ሐ ስድስት ሺ: ፷፻ ረ. ሁለት ሺ ሰላሳ ስምንት: ፳፻፴፰

## የምዕራፍ 1 ማጠቃለያ መልመጃ መልሶች

1. ሀ. እውነት ለ. እውነት ሐ. ሀሰት መ. ሀሰት
   ሠ እውነት ረ ሀሰት ሰ ሀሰት
2. 13,000፣ 14,000፣ 15,000፣ 16,000 ፣17,000 እና 18,000

3. 40,000፣ 50,000፣ 60,000፣ 70,000፣ 80,000 እና 90፣000
4. 300,000፣ 400,000፣ 500,000 እና 600,000
5. ሀ. ሀያ አምስት ሺ ስምንት መቶ ዘጠኝ
   ለ. ሶስትመቶ ሰባ ስምንት ሺ ሰድስት
   ሐ. ስምንት መቶ አርባ ስድስት ሺ ዘጠኝ መቶ ስምንት
   መ. አንድ ሚሊዮን
6. ሀ 909,003 ለ 540,064
   ሐ 110,001 መ 700,002
7.

| ተ/ቁ | የመቶ ሺ ቤት | የአስር ሺ ቤት | የሺ ቤት | የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | | 3 | 5 | 8 | 0 | 4 |
| ለ | 2 | 7 | 8 | 1 | 5 | 3 |
| ሐ | 4 | 4 | 6 | 9 | 9 | 8 |
| መ | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 2 |

8. ሀ 584,126 ____>____ 579,368

   ለ 800,001 ____<____ 800,004

   ሐ 99,682 ____<____ 994,657

   መ 828,414 ____=____ 828,414

   ሠ 792,466 ____>____ 792,366

9. ከትንሹ ወደ ትልቁ

   ሀ. 246,675፣ 346,525፣ 442,253፣ 568,489፣723,947

   ለ. 446,674፣ 642,252፣746,524፣ 868,480፣ 923፣842

   ሐ. 346,255፣546,882፣ 646,249፣ 746,878 ፣946,528

   መ. 946,247፣ 946,258፣ 946,481፣946,524፣946,875

10. ከትልቁ ወደ ትንሹ

ሀ. 723,947፣ 568,489፣ 442,253፣ 346525፣246,675

ለ . 923,842፣ 868,480፣ 746524፣ 642,252፣446,674

ሐ. 946,528፣ 746,878፣646,249፣ 546,882፣346,528

መ. 946,875፣ 946,524፣946,481፣946,258 ፣946,247

11. ሀ ፱ ለ ፲፮ ሐ ፳፫ መ ፴፯ ሠ ፵፪ ሰ ፶፯ ሸ ፷፬ ቀ ፸፩

12. ሀ አራት ለ አስራ አምስት ሐ ሰላሳ አምስት

መ ሀያ አራት ሠ ሰባ

13.

| ተ/ቁ | ወደ መቶ ሺ ቤት ሲጠጋጋ | የአስር ሺ ቤት ሲጠጋጋ | የሺ ቤትሲጠጋጋ | የመቶ ቤትሲጠጋጋ | የአስር ቤት ሲጠጋጋ | አሀዝ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | 0 | 10,000 | 9,000 | 8,800 | 8850 | 8,849 |
| ለ | 0 | 0 | 4,000 | 4,400 | 4400 | 4,397 |
| ሐ | 0 | 0 | 1,000 | 800 | 770 | 765 |
| መ | 0 | 50,000 | 46,000 | 45,600 | 45640 | 45,638 |
| ሠ | 100,000 | 70,000 | 68,000 | 68,500 | 68,470 | 68,462 |
| ረ | 600,000 | 580,000 | 583,000 | 582,700 | 582750 | 582,745 |
| ሰ | 200,000 | 200,000 | 198,000 | 198,200 | 198190 | 198,186 |

14

| ተ/ቁ | የመቶ ሺ ዎች | የአስር ሺዎች | የሺዎች | መቶዎች | የአስሮች | የአንዶች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | 7 | 6 | 9 | 4 | 3 | 1 |
| ለ | 8 | 0 | 1 | 2 | 0 | 9 |
| ሐ | 9 | 3 | 7 | 6 | 4 | 5 |
| መ | | | | 8 | 9 | 3 |
| ሠ | | | 1 | 8 | 9 | 7 |

ሀ$(1 \times 100000) + (4 \times 10000) + (6 \times 1000) + (8 \times 100) + (6 \times 10) + (7 \times 1\ )$

ለ$(4 \times 100000) + (2 \times 10000) + (8 \times 1000) + (5 \times 100) + (0 \times 10)\ + (6 \times 1)$

ሐ$(8 \times 100000) + (9 \times 10000) + (9 \times 1000) + (2 \times 100) + (5 \times\ + (3 \times 1)$

መ$(9 \times 100000) + (1 \times 10000) + (8 \times 1000) + (5 \times 100) + (3 \times 1)\ + (2 \times 1)$

14. ሀ 87,743 ለ 944,222 ሐ 782479 መ 141,464
15. በጥር ወር ከፍተኛ ጎብኚ ተመዘገበ
16. በ3ኛው ዙር

# ምዕራፍ ሁለት

## እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ 21

## መግቢያ

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ማስተማር ዉጤቶች:-

- ❖ እስከ 1,000,000 የሚደርሱ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር፡፡
- ❖ እስከ 1,000,000 የሚደርሱ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ፡፡

### ምዕራፉን ለማስተማር በዋናነት የሚያስፈለጉ የትምህርት መሳሪያዎች

- ➢ የተለየዩ ቀለማት ያሏቸዉ ጠመኔዎች እና ማርከሮች
- ➢ ክላሰር እና የስዕል ወረቀቶች
- ➢ የመደመር የቅይይር እና የተጣማጅነት ባህሪያት በትልቁ የተፃፈበት ክላሰር ወይም የስዕል ወረቀት

## 2.1 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች መደመር

ክፍለ ጊዜ 8

### 2.1.1 የንዑስ ርዕስ የመማር ብቃት:-

- ➢ እስከ 1000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር፡፡

### 2.1.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት የቀረቡ የመማር ማስተመር ዘዴ እና ተግባራቸዉ

እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር ባለፈዉ ንዑስ ርዕስ 2.1.1 ላይ ተምረዋል፡፡ ነገር ግን መምህር ተማሪዎች የተማሩትን ምን ያህል እንደሚያስታዉሱ ለማወቅ በተግባር 1 ላይ ያሉትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጓቸዉ፡፡ ሲጨርሱ የሰሩትን ወጥተዉ እንዲሰሩ ያድርጓቸዉ፡፡ እባክዎትን መምህር ከዚህ በተጨማሪ የሚከተሉትን የማሰተማር ስልቶች ይጠቀሙ፡፡

- ➢ ተማሪዎች ቁጥሮችን በመነጣጠልና በማጣመር 10 እንዲያመጡ ማገዝ

ምሳሌ፡ $7 + 9 = 6 + 1 + 9 = 6 + 10 = 16$

- ➢ ተማሪዎች በመደመር ጊዜ የቤት ዋጋ እንዲጠቀሙ መርዳት
- ➢ ተማሪዎች የሚከተሉትን ሂደቶች (ዘዴዎች) እንዲከተሉ ማገዝ

- አስሮችን እና አንዶችን መደመር እና ማጣመር
- አስር ለማድረግ የተወሰነ ቁጥር ከሌላዉ መዉሰድ

$56 + 48 = 54 + 50 = 104$

$56 + 48 = 56 + 50 - 2 = 104$

- ቁጥሮችን በመደመርና በትንተና መጠቀም

$358 + 459 = 300 + 400 + 50 + 50 + 8 + 9 = 700 + 100 + 17$

### 2.1.3 የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

መምህር! የዚህን ንዑስ ክፍል ምዘና የሚተገበርባቸዉ ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

- ተማሪዎች እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁሮችን እንዲደምሩ ጥያቄ መጠየቅ
- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መሰረት ያደረገ ተግባራዊ ፕሮብሌሞችን መስራት
- በምልከታ እና በወረቀት ሙከራ መስጠት
- የተማሪዎች ውጤት እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ-መልስ መስጠት

### 2.1.4 የተግባርና የመልመጃ መልሶች ከነማብራሪያቸው

#### የተግባር 1 መልሶች

1. ሀ $4,672 + 1,000 = 5,672$      ለ $856,724 + 34,577 = 891,301$

መምህር! ከመልመጃ 1 ጥያቄዎች በመምረጥ የቤት ስራ፣ የክፍል ስራ እና የቡድን ስራ በመስጠት እንዲሰሯቸዉ ማድረግ፡፡ የክፍል ስራዉን ግን የመስሪያ ሰዓት በመስጠት በሰጡት ሰዓት ዉስጥ የጨረሱትን ተማሪዎች ደብተር በማረም ደብተራቸዉ ላይ የተማሪዎችን ሞራል የሚገነባ አስተያት ይፃፉበት፡፡ በሚቀጥለዉ ክ/ጊዜ የተሰጡትን የቤት ሥራ መስራት አለመስራታቸዉን በማረጋገጥ ተማሪዎች የሰሩትን የቤት ስራ በየተራ እየወጡ ጥቁር ሰሌዳዉ ላይ እንዲሰሩ ማበረታታት እና ሞራል መስጠት፡፡ ተማሪዎች ከስሩት መልስ ላይ በመነሳት ማስተካከያ እና ባብራሪያ መስጠት፡፡

#### የመልመጃ 1 መልሶች

1. ሀ. $12 + 4 = 10 + 2 + 4 = 10 + 6 = 16$

   ለ. $8 + 9 = 7 + 1 + 9 = 7 + 10 = 17$

   ሐ. $14 + 5 = 10 + 4 + 5 = 10 + 9 = 19$

2. ሀ. $64 + 28 = 60 + 4 + 20 + 8 = 60 + 20 + 8 + 4$

   $= 80 + 12$

   $= 92$

ለ. 57 + 93 = 50 + 7 + 90 + 3

= 50 + 90 + 7 + 3

= 140 + 10

= 150

ሐ. 75 + 84 = 70 + 5 + 80 + 4

= 70 + 80 + 5 + 4

= 150 + 9

= 159

3. ሀ. 951 + 850 = 900 + 50 + 1 + 800 + 50

= 900 + 800 + 50 + 50 +1

= 1700 +100 +1

= 1800 +1

= 1801

ለ. 3,261 + 6,845

= 3,000 + 200 + 60 + 1 + 6,000 + 800 + 40 + 5

= 3,000 + 6,000 + 200 + 800 + 60 + 40 + 1 + 5

= 9,000 + 1,000 + 100 + 6

= 10,000 + 100 +6

= 10,106

ሐ. 216,760 + 64,412

= 200,000+10,000+6000+700+60+60,000+4000+400+10+2

= 200,000+10,000+60,000+6000+4000+700+400+60+10+2

= 200,000 +70,000 +10,000 1,100 + 70 +2

= 200,000 + 80,000 + 1,170 + 2

= 281,172

4. ሀ. 376 + 622 = 998

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 3 | 7 | 6 |
| + | 6 | 2 | 2 |
| = | 9 | 9 | 8 |

ለ. 6,562 + 5,354=11,916

| አለኝ | +1 | +1 | +1 | |
|---|---|---|---|---|
| | 6 | 5 | 6 | 2 |
| + | 5 | 3 | 5 | 4 |
| = | 11 | 9 | 1 | 6 |

ሐ. 631,286 + 331,989 = 963,275

| አለኝ | | | +1 | +1 | +1 | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 6 | 3 | 1 | 2 | 8 | 6 |
| + | 3 | 3 | 1 | 9 | 8 | 9 |
| = | 9 | 6 | 3 | 2 | 7 | 5 |

መ 821,286+127,579 = 948,865

| አለኝ | | | | +1 | +1 | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 8 | 2 | 1 | 2 | 8 | 6 |
| + | 1 | 2 | 7 | 5 | 7 | 9 |
| = | 9 | 4 | 8 | 8 | 6 | 5 |

5.

| ሀ | ለ | ሀ+ለ | ለ+ሀ |
|---|---|---|---|
| 100,000 | 30,000 | 130,000 | 130,000 |
| 566,722 | 366,657 | 933,379 | 933,379 |

## 2.2 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

### ክፍለ ጊዜ 9

### 2.2.1 የንዑስ ርዕስ ብቃት

❖ እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

### 2.2.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴና ተግባራት

ተማሪዎች ምን ያህል መቀነስን እንደሚችሉ ለመለየት በተግበር 2 ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጓቸው፡፡ ጥቂዎቹን ተወያይተው ሲጨርሱ ለተወሰኑ ቡድኖች መስጠት እና ከቡድኖቹ አንድ አንድ ተማሪ ወጥተው እንዲያስረዱ ያድርጓቸው፡፡

## 2.2.3 የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

- ❖ ሙሉ ቁጥሮችን እንዲቀንሱ ጥያቄዎችን በመስጠት በግል እንዲሰሩ ማድረግ
- ❖ ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ-መልስ በመስጠት ማበረታታት፣ ምልከታ ማድረግ ወይም የወረቀት ሙከራ መስጠት

## 2.2.4 የተግባርና መልመጃ መልሶች ከነማብራሪያቸው

### የተግባር 2 መልሶች

1. ሀ 6,321−340 ለ 547,389−64,278

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 6,321 | 547,389 |
| − 340 | − 64,278 |
| = 5,981 | = 483,111 |

መምህር! እስኪ ተማሪዎች ሙሉ ቁጥሮችን ለማባዛት የተማሯቸዉን የተለያዩ የማባዛት ስልቶችን ማወቃቸውን ለመገመገም ከመልመጃ 2 ጥያቄዎችን በመምረጥ የቤት ስራ፣ የክፍል ስራ እና የቡድን ስራ በመስጠት እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ የክፍል ስራዉን ግን የመስሪያ ሰዓት በመስጠት በሰጡት ሰዓት ዉስጥ የጨረሱትን ተማሪዎች ደብተር በማረም ደብተራቸዉ ላይ የተማሪዎችን ሞራል የሚገነባ አስተያት ይፃፉበት፡፡ በሚቀጥለዉ ክ/ጊዜ የተሰጡትን የቤት ሥራ መስራት አለመስራታቸዉን በማረጋገጥ ተማሪዎች የሰሩትን የቤት ስራ በየተራ እየወጡ ጥቁር ሰሌዳዉ ላይ እንዲሰሩ ማበረታታት እና ሞራል መስጠት እንዲሁም ተማሪዎች ከስሩት መልስ ላይ በመነሳት ማስተካከያ እና ማብራሪያ ይስጡ፡፡

### የመልመጃ 2 መልሶች

1. ሀ 78,246 −11,111 = 67,135

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 7 | 8 | 2 | 4 | 6 | ዋና |
| − | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | ተቀናሽ |
| = | 6 | 7 | 1 | 3 | 5 | ልዩነት |

ለ 771,234 −342,531 = 428,703

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 6 | 10 | 12 | | | |
| | 7 | ~~7~~ | ~~1~~ | ~~2~~ | 3 | 4 | ዋና |
| − | 3 | 4 | 2 | 5 | 3 | 1 | ተቀናሽ |
| = | 4 | 2 | 8 | 7 | 0 | 3 | ልዩነት |

ሐ. 678,803– 569,740 = 109,063

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 6 | 18 | 7 | 10 | | |
| | 6 | ~~7~~ | ~~8~~ | ~~8~~ | ~~0~~ | 3 | ዋና |
| – | 5 | 6 | 9 | 7 | 4 | 0 | ተቀናሽ |
| = | 1 | 0 | 9 | 0 | 6 | 3 | ልዩነት |

መ. 971,204 – 342,535 = 628,669

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 6 | 100 | 11 | 10 | | |
| | 9 | ~~7~~ | ~~1~~ | ~~2~~ | ~~0~~ | 4 | ዋና |
| – | 3 | 4 | 2 | 5 | 3 | 5 | ተቀናሽ |
| = | 6 | 2 | 8 | 6 | 6 | 9 | ልዩነት |

ሠ. 896,543– 672,348 = 224,195

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 4 | 13 | 13 | |
| | 8 | 9 | 6 | ~~5~~ | ~~4~~ | 3 | ዋና |
| – | 6 | 7 | 2 | 3 | 4 | 8 | ተቀናሽ |
| = | 2 | 2 | 4 | 1 | 9 | 5 | ልዩነት |

2

| ሀ | ለ | ሀ – ለ = መ |
|---|---|---|
| 500,000 | 100,000 | 400,000 |
| 900,000 | 98,000 | 802,000 |

## 2.3 ሙሉ ቁጥሮች መሰረት ያደረገ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት

### ክፍለ ጊዜ 4

### 2.3.1 የንዑስ ርዕስ የመማር ብቃት፡-

- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች መሰረት ያደረገ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት

## 2.3.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት የቀረቡ የመማር ማስተመር ዘዴ እና ተግባራቸዉ

ተማሪዎች በ3ኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርር ላይ የቃላት ፐሮብሌሞችን መፍታት ተምረዋል፡፡ ነገር ግን ምን ያህል እንደሚያስታዉሱ በተግበር 3 ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጓቸው፡፡ ጥያቄዎቹን ተወያይተው ሲጨርሱ ለተወሰኑ ቡድኖች እድል መስጠት እና ከቡድኖቹ አንድ ተማሪ ወጥተው እንዲያስረዱ ያድርጉ፡፡

## 2.3.3 የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መሰረት ያደረገ የቃላት ፐሮብሌሞችን መስጠት በምልከታ እና በወረቀት ሙከራ መስጠት

የተማሪዎች ውጤች እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ-መልስ መስጠት

## 2.3.4 የተግባርና የመልመጃ መልሶች ከነማብራሪያቸው

### ተግባር 3 መልሶች

1. ግንዛቤ ይወስዳሉ ተብሎ የተለዩ ተማሪዎች ብዛት = 205,985 ተማሪዎች

ግንዛቤ የወሰዱ ተማሪዎች ብዛት = 150,849 ተማሪዎች ግንዛቤ ያላገኙ ተማሪዎች ብዛት = 205,985 – 150,849 = 55,136 ናቸዉ፡፡

መምህር! ከመልመጃ 3 ጥያቄዎች በመምረጥ የቤት ስራ፣ የክፍል ስራ እና የቡድን ስራ በመስጠት እንዲሰሯቸዉ ማድረግ፡፡ የክፍል ስራዉን ግን የመስሪያ ሰዓት በመስጠት በሰጡት ሰዓት ዉስጥ የጨረሱትን ተማሪዎች ደብተር በማረም ደብተራቸዉ ላይ የተማሪዎችን ሞራል የሚገነባ አስተያት ይፃፉበት፡፡

በሚቀጥለዉ ክ/ጊዜ የተሰጡትን የቤት ሥራ መስራት አለመስራታቸዉን በማረጋገጥ ተማሪዎች የሰሩትን የቤት ስራ በየተራ እየወጡ ጥቁር ሰሌዳዉ ላይ እንዲሰሩ ማበረታታት እና ሞራል መስጠት፡፡ ተማሪዎች ከስሩት መልስ ላይ በመነሳት ማሰተካከያ እና ማብራሪያ መስጠት፡፡

### የመልመጃ 3 መልሶች

1. ጠቅላላ የተማሪ ብዛት = 3,769

በበጎ አድራጎት ክበብ የሚሳተፉ ተማሪዎች = 847

በነገው ሰው መምህር ክበብ የሚሳተፉ ተማሪዎች = 543

በአካባቢ እንክብካቤ ክበብ የሚሳተፉ ተማሪዎች = 719

ሀ በሁሉም ክበቦች ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች

= 847 + 543 + 719 =2,109 ተማሪዎች

ለ የትኛዉም ክበብ ውስጥ ያልተሳተፉ ተማሪዎች

= 3,769 – 2,109 = 1,660 ተማሪዎች

2. ዋና = 12,347፣ ልዩነት = 2,630

ትንሹ ሙሉ ቁጥር = ተቀናሽ = ዋና – ልዩነት

= 12,347– 2,630 = 9,717 ትንሹ ቁጥር ነዉ።

3. የሁለት ሙሉ ቁጥሮች ልዩነት 15,984 ነዉ። ትንሹ ሙሉ ቁጥር 480,963 ነዉ። ትልቁ ሙሉ ቁጥር ስንት ነዉ?

ልዩነት =15,984 ተቀናሽ =480,963

ዋና= ተቀናሽ + ልዩነት = 480,963 + 15,984 = 496,947

4. ስልጠና ከመውሰዱ በፊት በአመት የሚከፈል ብር = 450,984 ብር

ከስልጠና ከወሰደ በኋላ በአመት የሚከፈል ብር = 288,916 ብር

ድርጂቱ በአመት የቆጠበዉ ብር = 450,984 – 288,916 = 162,068 ብር ይሆናል።

## የምዕራፍ 2 የማጠቃለያ መልመጃ መልሶች

1. ሀ. እዉነት ለ. ሀሰት ሐ. ሀሰት መ. እዉነት

2. ሀ 413 + 15 = 428 ሐ. 3,648 + 236 = 3,884

ለ 978 + 215,895 = 216,873 መ 941,809 + 58,191 =1,000,000

3. ሀ 4,000 – 346 = 3,654 ሐ 247,365 – 132,151 = 115,214

ለ 36,375 –19,320 = 17,055 መ 996,370 – 293,478 = 702,892

4. 200,000 –19,897 =180,103 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ተሰራጭቷል።

5. በ2ኛው ዙር. ይህም 1,871–1,843 = 28

6. 190,000–180,000 =10,000

# ምዕራፍ ሦስት

## እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት እና ማካፈል

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ 44

## መግቢያ

ተማሪዎች በምዕራፍ 2 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ እና መደመር እንዲያስታውሱ የተለያዩ ጥያቄዎች በቡድን እና በግል በመስጠት ለተማሪዎቹ ይከልሱላቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት እንደሚማሩ ለተማሪዎች ሞራላቸዉን በሚያነቃቃ መልኩ ይንገሯቸዉ፡፡

### ከምዕራፉ የመማር ውጤቶች:-

- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት ይችላሉ፡፡
- ማባዛትን መሰረት ያደረጉ ተግባራዊ የቃላት ፕሮብሌሞችን ይፈታሉ

### ምዕራፉን ለማስተማር በዋናነት የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች

- የማባዛት የቁጥር ቤት ሰንጠረዥ
- የተለየያዩ ቀለማት ያላቸዉ ጠመኔዎች እና ማረከሮች
- የስዕል ወረቀት ወይም ክላሰር
- የማባዛት የቅይይር እና የተጣማጅነት ባህሪያት በትልቁ የተፃፈበት የስዕል ወረቀት ወይም ክላሰር
- የቃላት ፕሮብሌሞችን ለመፍታት የሚያስፈለጉ የአሰራር ደረጃዎችን የሚያሳይ በትልቁ በስዕል ወረቀት ላይ የተፃፉ ፅሁፎች

## 3.1 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት (21)

### 3.1.1 እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማባዛት

### ክፍለ ጊዜ 3

#### 3.1.1.1 የንዑስ ርእስ የመማር ብቃቶች

- ❖ እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ማባዛት
- ❖ እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ10 ማባዛት

## 3.1.1.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴና ተግባራት

በመጀመርያ በተግባር 1 ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጉ፡፡ ጥያቄዎቹን ተወያይተው የሰሩትን ወጥተዉ እንዲሰሩ ያበረታቷቸዉ፡፡

መምህር! እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ማባዛት መቻል አለመቻላቸዉን ለመገመገም ከመልመጃ 1 ጥያቄዎች በመምረጥ የቤት ስራ፣ የክፍል ስራ እና የቡድን ስራ በመስጠት እንዲሰሯቸዉ ማድረግ፡፡ የክፍል ስራዉን ግን የመስሪያ ሰዓት በመስጠት በሰጡት ሰዓት ዉስጥ የጨረሱትን ተማሪዎች ደብተር በማረም ደብተራቸዉ ላይ የተማሪዎችን ሞራል የሚገነባ አስተያየት ይፃፉበት፡፡ በሚቀጥለዉ ክ/ጊዜ የተሰጡትን የቤት ሥራ መስራት አለመስራታቸዉን በማረጋገጥ ተማሪዎች የሰሩትን የቤት ስራ በየተራ እየወጡ ጥቁር ሰሌዳዉ ላይ እንዲሰሩ ማበረታታት እና ሞራል መስጠት፡፡ ተማሪዎች ከስሩት መልስ ላይ በመነሳት ማስተካከያ መስጠት እና ማብራሪያ መስጠት፡፡

### የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

- የ100 እና 1,000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ እንዲያበዙ ተማሪዎችን መጠየቅ
- ተማሪዎች የተለያዩ የማባዛት ዘዴዎችን በሂሳባዊ ስሌቶች ቅደም ተከተል እንዲጠቀሙ ማገዝ
- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ከሙሉ ቁጥሮች ጋር እንዲያባዙ መጠየቅ
- ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ-መልስ በመስጠት ማበረታታት፣ ምልከታ ማድረግ ወይም የወረቀት ሙከራ መስጠት

### የተግባርና የመልመጃ መልሶች ከነማብራሪያቸው

#### የተግባር 1 መልሶች

1. ሀ $20 \times 4 = 80$     ሐ $450 \times 2 = 900$

   ለ $100 \times 3 = 300$     መ $83 \times 8 = 664$

2. ተማሪዉ በአንድ ሳምንት ለገበያ የሚያቀርበዉ የእንቁላል ብዛት=18

   በ 9 ሳምንት ለገበያ የሚያቀርበዉ እንቁለል ብዛት፡ $18 \times 9 = 162$

## የመልመጃ 1 መልሶች

1. ሀ. 100   ለ. 900   ሐ. 832   መ.  445   ሠ.686
2. ሀ $684 = 600 + 80 + 4 = 100\times6 + 10\times8 + 4\times1$

   ለ $789 = 700 + 80 + 9 = 100\times7 + 10\times8 + 9\times1$

   ሐ $843 = 800 + 40 + 3 = 100\times8 + 10\times4 + 3\times1$

   መ $980 = 900 + 80 + 0 = 100\times9 + 10\times8 + 0\times1$
3. ሀ $54\times 2 = (50 + 4)\times2 = (50\times2) + (4\times2) = 100 + 8 = 108$

   ለ $302\times3 = (300 + 2)\times3 = (300\times3) + (2\times3) = 900 + 6 = 906$

   ሐ $82\times 4 = (80 + 2)\times4 = (80\times4) + (2\times4) = 320 + 8 = 328$

   መ $98\times5 = (90 + 8)\times5 = (90\times5) + (8\times5) = 450 + 40 = 490$

   ሠ $175\times 6 = (100 + 70 + 5)\times6$

   $= (100\times6) + (70\times6) + (5\times6) = 600 + 420 + 30 = 1{,}050$
4. በ1 ሳምንት $= 129$ ብር

   በ7 ሳምንታት $=?$

   $7\times129 = 903$ ብር

   ስለዚህ በ7 ሳምንታት 903 ብር ይሸጣሉ፡፡

## የተግባር 2 መልሶች

1. ሀ $9\times 10 = 90$   ለ. $10\times10 = 100$

   ሐ $50\times0 = 0$   መ $80\times 10 = 800$
2. $5 \times 10 = 50$ ሰዓታት

መምህር! እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ10 ማባዛት መቻል አለመቻላቸዉን ለመገመገም ከመልመጃ 2 ጥያቄዉች በመምረጥ የቤት ስራ፣ የክፍል ስራ እና የቡድን ስራ በመስጠት እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ የክፍል ስራዉን የመስሪያ ሰዓት በመስጠት በሰጡት ሰዓት ዉስጥ የጨረሱትን ተማሪዎች ደብተር በማረም የተማሪዎችን ሞራል የሚገነባ አስተያት ይጻፉበት፡፡

## የመልመጃ 2 መልሶች

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በ10 አባዙ፡፡

   ሀ $64\times10 = 640$   ለ $302\times10 = 3{,}020$

   ሐ $982\times10 = 9{,}820$   መ $598\times10 = 5{,}980$

   ሠ $775\times10 = 7{,}750$
2. $658\times10 = 6{,}580$

## 3.1.2 ሙሉ ቁጥሮችን የማባዛት ስልቶች

### ክፍለ ጊዜ 3

### የንዑስ ርዕስ የመማር ብቃት

- የተለያዩ የማባዛት ስልቶችን በመጠቀም ቁጥሮችን ማባዛት

### ንዕስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴና ተግባራት

ተማሪዎቸ ምን ያህል የማባዛት ስልቶችን እንደሚያዉቁ ለመለየት በተግበር 3 ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጓቸው፡፡ ጥያቄዎቹን ተወያይተው ሲጨርሱ ለተወሰኑ ቡድኖች እድል መስጠት እና ከቡድኖቹ አንድ አንድ ተማሪዎች ወጥተው እንዲያስረዱ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ የማባዛት ዘዴዎችን በሂሳባዊ ስሌቶች ቅደም ተከተል እንዲጠቀሙ ማገዝ፡፡ በተጨማሪ ከመልመጃ 3 ውስጥ የተወሰኑ ጥያቄዎች በመምረጥ የቤት ስራ በመስጠት የማባዛት ስለቶችን በሚገባ እንዲያዉቁ ያድርጓቸዋል፡፡

### የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

- ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ በመስጠት ማበረታታት ምልከታ ማድረግ ወይም የወረቀት ሙከራ መስጠት፡፡

<u>**የማነቃቂያ ጥያቄዎች፡-**</u> ተማሪዎች! ከዚህ በታች የተሰጠውን የማነቃቂያ ጥያቄ እንዲሰሩና ሌሎች እርሶ የሚያውቋቸው ካሉ በክፍል ውስጥ ያስተምሩ፡፡

**በ9 ማባዛት**: ድምራቸው 9,

የ9 አስገራሚ እውነታዎች ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?

| × | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | 18 | 27 | 36 | 45 | 54 | 63 | 72 | 81 | |
| | | | | | | | | | |
| መደመር | 1+8 | 2+7 | 3+6 | 4+5 | 5+4 | 6+3 | 7+2 | 8+1 | |
| ድምር | 9 | 9 | 9 | 9 | 9 | 9 | 9 | 9 | |

ከ2 እስከ 9 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ስናበዛ የብዜቱን አስረኛ ቤትና አንደኛ ቤት ስንደምራቸው 9 ይሆናሉ። ማንኛውንም ባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር በ 9 ለማባዛት የ10ኛ ቤት ዋጋው ከ2 እስከ 9 ባሉት ላይ 1 በመቀነስ ሲገኝ የ1ኛ ቤት ዋጋው 9- ከላይ ያገኘነው ሙሉ ቁጥር በመፃፍ ይገኛል።

ለምሳሌ፡-$5 \times 9$፣ እና $9 \times 9$፣ እንመልከት

$5-1=4$ →10ኛ ቤት ዋጋ $9-1=8$ →10ኛ ቤት ዋጋ

$9-4=5$ →1ኛ ቤት ዋጋ $9-8=1$ →1ኛ ቤት ወጋ

ስለዚህ ብዜቱ 45 ይሆናል። ስለዚህ ብዜቱ 81 ይሆናል።

### 3.1.2.3 መልሶች ከነማብራሪያቸው

#### የተግባር 3 መልሶች

1. እባክዎትን መምህር የማባዛትን ስልቶችን ለተማሪዎች በዝርዝር ይፃፉላቸዉ። ለምሳሌ፡ ከፋፍለን ማባዛት፣ በሰንጠረዥ ማባዛት፣ በመስመር እና በቁልቁል ማባዛት።

#### የመልመጃ 3 መልሶች

1. ሀ.$700 \times 2=$1,400 ሐ.$436 \times 5=$2,180

ለ.$741 \times 9=$6,669 መ $1245 \times 3=$3,735

ሠ.$972 \times 8=$7,776 ረ.$8,152 \times 7=$57,064

## 3.1.3 እስከ 10,000 ያሉ የ1000 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ እና በ10 ማባዛት

#### ክፍለ ጊዜ 3

### 3.1.3.1 የንዑስ ምዕራፍ የመማር ብቃት

- ብዜታቸው ከ10,000 በታች የሆኑ የ100 እና የ1,000 ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት

### 3.1.3.2 ንዕስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴና ተግባራት

❖ እባከዎት መምህር ተማሪዎች በተግበር 4 ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጓቸው። ጥያቄዎቹን ተወያይተው ሲጨርሱ ለተወሰኑ ቡድኖች መስጠት እና ከቡድኖቹ አንድ አንድ ተማሪዎች ወጥተው እንዲያስረዱ ያድርጓቸው። ተማሪዎች እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ እና በ10 እንዲያባዙ ያግዟቸው።

### 3.1.3.3 የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

❖ ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ በመስጠት ማበረታታት ምልከታ ማድረግ ወይም የወረቀት ሙከራ መስጠት፣ የቤት ስራ፣ የክፍል ስራ መሰጠት።

### 3.1.3.4 የተግባር እና የመልመጃ መልሶች ከነማብራሪያቸው

#### የተግባር 4 መልሶች

1. 1,000፣ 2,000፣ 3,000፣ 4,000፣ 5,000፣ 6,000፣ 7,000፣ 8,000 እና 9,000

መምህር! እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ማባዛት መቻል አለመቻላቸዉን ለመገመገም ከመልመጃ 4 ጥያቄዉች በመምረጥ የቤት ስራ፣ የክፍል ስራ እና የቡድን ስራ በመስጠት እንዲሰሩ ማድረግ። የክፍል ስራዉን ግን የመስሪያ ሰዓት በመስጠት በሰጡት ሰዓት ዉስጥ የጨረሱትን ተማሪዎች ደብተር በማረም ደብተራቸዉ ላይ የተማሪዎችን ሞራል የሚገነባ አስተያት ይፃፉበት። በሚቀጥለዉ ክ/ጊዜ የተሰጡጥን የቤት ሥራ መስራት አለመስራታቸዉን በማረጋገጥ ተማሪዎች የሰሩትን የቤት ስራ በየተራ እየወጡ ጥቁር ሰሌዳዉ ላይ እንዲሰሩ ማበረታታት አና ሞራል መስጠት። ተማሪዎች ከስሩት መልስ ላይ በመነሳት ማሰተካከያ እና መብራሪያ መስጠት።

#### የመልመጃ 4 መልሶች

1. ሀ 1000 × 9 =9,000     ሐ 1400 × 7= 9,800

   ለ 5,000 ×1= 5,000     መ 1500 × 4 = 6,000

   ሠ 2000 ×0= 0

#### ተግባር 5 መልሶች

1. ሀ. 2,000× 10 = 20,000

   ለ 6,000× 10 = 60,000     ረ 7,000× 10 = 70,000

መምህር! እስከ 10,000 ያሉ የ1000 ብዜቶችን በ10 ማባዛት መቻል አለመቻላቸዉን ለመገመገም ጥያቄዎች በመምረጥ የቤት ስራ፣ የክፍል ስራ እና የቡድን ስራ ይስጧቸው። ለጨረሱትን ተማሪዎች ደብተር በማረም ደብተራቸዉ ላይ የተማሪዎችን ሞራል የሚገነባ አስተያት ይፃፉበት።

### የመልመጃ 5 መልሶች

1. ሀ. 2,000× 10 = 20,000

   መ. 1,000× 10 = 10,000

   ረ. 9,000 × 10 = 90,000

2. 5,000፣ 6,000፣ 7,000፣ 8,000 እና 9,000

## 3.1.4 እስከ 100,000 ያሉ የ10,000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማባዛት

### ክፍለ ጊዜ 3

### 3.1.4.1 የንዑስ ርዕስ የመማር ብቃቶች

- ❖ እስከ 100,000 ያሉ የ10,000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ ማባዛት
- ❖ እስከ 100,000 ያሉ የ10,000 ብዜቶችን በ10 ማባዛት

### 3.1.4.2 ንዕስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴና ተግባራት

እባከዎት መምህር ተማሪዎቸ በተግበር 6 ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጓቸው፡፡ ጥያቄዎቹን ተወያይተው ሲጨርሱ ለተወሰኑ ቡድኖች እድል መስጠት እና ከቡድኖቹ አንድ አንድ ተማሪዎች ወጥተው እንዲያስረዱ ያድርጓቸው፡፡

### 3.1.4.3 የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

- ❖ እስከ 100,000 ያሉ የ10,000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ እንዲያባዙ በግል የሚስሩ ጥያቄዎች መስጠት፡፡
- ❖ ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ-መልስ በመስጠት ማበረታታት፣ ምልከታ ማድረግ ወይም የወረቀት ሙከራ መስጠት

### 3.1.4.4 የተግባርና የመልመጃ መልሶች

#### የተግባር 6 መልሶች

1. ሀ 10,000 ×4 = 40,000

   ሐ 70,000 ×4 = 280,000

   ረ 90,000 ×4 = 360,000

### የመልመጃ 6 መልሶች

1. ሀ 10,000 × 6 = 600,000

   ለ 30,000 × 6 = 180,000

   መ 70,000 × 6 = 420,000

2. 30,000፣ 40,000 እና 50,000 ናቸዉ፡፡

   በመቀጠል በ8 ማባዛት

   30,000 × 8 = 240,000

   40,000 × 8 = 320,000

   50,000× 8 = 400,000

3. ሀ 60,000 × 3=180,000

   ለ 20,000 × 5= 100,000

   ሐ 70,000 × 4= 280,000

   መ 100,000 × 9= 900,000

## 3.1.5 ብዜታቸው እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማባዛት

#### ክፍለ ጊዜ 3

### 3.1.5.1 የንዑስ ርእስ የመማር ብቃት

➢ ብዜታቸዉ እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለአንድ ሆሄ ማባዛት

### 3.1.5.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴና ተግባራት

እባክዎት መምህር ተማሪዎቻ በተግበር 7 ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩባቸው ያድርጓቸው፡፡ ጥያቄዎቹን ተወያይተው ሲጨርሱ ለተወሰኑ ቡድኖች መስጠት እና ከቡድኖቹ አንድ አንድ ተማሪዎች ወጥተው እንዲያስረዱ ያድርጉ፡፡

ለምሳሌ፡- የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ብዜታቸዉን ፈልጉ፡፡

ሀ 235 × 9 ለ 3,020 × 7

### 3.1.5.3 የምዘና ስልቶች እና ዝርዝር ተግባራት

- እስከ 1000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ከሙሉ ቁጥሮች ጋር እንዲያባዙ መጠየቅ

- ተማሪዎች የመማር ዉጤታቸዉ እንዲሻሻል ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ በመስጠት ማበረታታት ምልከታ ማድረግ ወይም የወረቀት ሙከራ መስጠት

## 3.1.5.4 የተግባር እና የመልመጃ መልሶች ከነማብራሪያቸዉ

### የተግባር 7 መልሶች

1. የእርዳታ ድርጂቱ የለገሰዉ ጤፍ ዱቄት በ1 ዙር = 10,000 ኪ.ግ

በ9 ዙሮች = ?

ድርጂቱ ጠቅላላ የለገሰው በ9 ዙሮች= 10,000 × 9 ኪ.ግ ዱቄት = 90,000

መምህር! ብዜታቸው እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ እና በ10 ማባዛት መቻል አለመቻላቸዉን ለመገመገም የተለያዩ ጥያቄዎች በመምረጥ የቤት ስራ፣ የክፍል ስራ እና የቡድን ስራ በመስጠት እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

### የመልመጃ 7 መልሶች

1. ሀ 715 ለ 21,714 ሐ 98,056
   መ 337,912 ሠ 900,009 ረ 940,900

2. ሀ $68 \times 8$ ___>___ $8 \times 64$

ለ $708 \times 3$ ___<___ $602 \times 4$

ሐ $9,312 \times 8$ ___<___ $10,306 \times 9$

መ $304,005 \times 3$ ___>___ $279,098 \times 2$

ሠ $450,000 \times 2$ ___=___ $300,000 \times 3$

### የተግባር 8 መልሶች

1. ሀ. $88 \times 22$ እና $22 \times 88$

$88 \times 22 = 1,936$ እና $22 \times 88 = 1,936$

ስለዚህ $88 \times 22 = 22 \times 88$ (የማባዛት የቅይይር ባህሪ ይባላል፡፡)

